የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ-ፍትህ ፓርቲ (ኢ-ዜማ)

ETHIOPIAN CITIZENS FOR SOCIAL JUSTICE PARTY (E-ZEMA)

Head Office ☐ Branch Office ☐ Support Group ☐

ቀን 08/04/2012 ዓ.ም
Date
ቁጥር ኢዜማ/0364/12
Ref.

ለክቡር ዶ/ር አብይ አህመድ

የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ቅሬታ ማቅረብን ይመለከታል

በኢትዮጵያዊያን ብርቱ መስዋዕትነት በተገኘው የለውጥ ሂደት ውስጥ የጠበበው ፖለቲካ ምህዳር ከመቼውም ጊዜ በላይ ሰፍቶ ዜጎች ሃሣባቸውን በነፃነት የሚገልፁበትን ምቹ ሁኔታን መፍጠር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ተግባር መሆኑ እሙን ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ የተለያዩ የህግ መሠረት ያላቸው አደረጃጀቶች በህገ-መንግስቱ ላይ በሰፈሩ ድንጋጌዎች መሰረት በየትኛውም የአገሪቱ ክፍሎች ተንቀሳቅሰው ሃሣባቸውን የመግለፅ ነፃነታቸው ሊጠበቅ ይገባል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) ከምስረታው ጀምሮ መዋቅር በመዘርጋትና ህዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ ሠላምና መረጋጋትን የማስፈን ሠፊ ፕሮግራም አውጥቶ በሁሉም ክልሎች እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይሁን እንጂ በኦሮሚያ በሚገኙ የምርጫ ወረዳዎች ግን ተደጋጋሚ ተግዳሮቶች እየገጠሙን ይገኛሉ ከነዚህ ውስጥ፡-

1ኛ. በምሥራቅ አርሲ ዞን በስሬ ወረዳ በተደጋጋሚ ህዝባዊ ስብሰባ ለማካሄድ ለሶስት ተከታታይ ሣምንታት ያቀረብነውን ጥያቄ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊዎች ሊቀበሉት ቀርቶ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮችን በቢሮአቸው ለማነጋገር እንኳን ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ከዚህ ባሻገር ስሬ ወረዳ ላይ የሚንቀሳቀሱትን የኢዜማን አመራርና አባላት በማዋከብና በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ ችግር በመፍጠር እስከ አሁን ድረስ ፕሮግራሙን እንዳናካሄድ ተደርገናል። በዚህ ጉዳይ ላይ የክልሉን ከፍተኛ አመራሮች በስልክ አግኝተን ያሳወቅናቸው ቢሆንም መፍትሄ ማግኘት ግን አልቻልንም።

2ኛ. በአዳማ ከተማ የግለሰብ ህንፃ ላይ ፓርቲውን ጽ/ቤት ለመክፈት ተነጋግረን፣ ገንዘብ ከፍለን ውል ከተዋዋልን በኋላ ከጨፌ ኦሮሚያ ደብዳቤ ካላመጣችሁ እውቅና አንሰጥም በሚል በከተማው ውልና ማስረጃ መ/ቤት ከፍተኛ መጉላላት ደርሶብናል።

3ኛ. በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለያዩ ጊዜያት ክልሉን የተመለከቱ የስብሰባና የውይይት ፕሮግራም ላይ ጥሪ እየተደረገላቸው ሌሎች ፓርቲዎች ሲገኙ ኢዜማን ባገለለ መልኩ መሆኑ ቅሬታ ፈጥሮብናል።

በአጠቃላይ ልንገነባ ለምናስበው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ኢዜማም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት እያጋጠሙን ያሉትን ተግዳሮቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጡን በአክብሮት እንጠይቃለን።

ከታላቅ አክብሮት ጋር!

የሺዋስ አሰፋ የኔሁን
የኢ-ዜማ ሊቀ-መንበር
Yeshiwas Assefa Yenehun
E-ZEMA Chairperson

Head Office +251 11 550 8727/28 +251 11 465 5765 +251 118 59 2950 +251 118 59 3006 +251 118 68 88 55
Mob 0944 10 76 59 /60 /61 +251 0118 722884